
# የመሪዎች ሴራ በኢትዮጵያ

/ አዲስ መጽሐፍ /





ETHIO BOOKS DELIVERY
order now
+251 923462526


## በቀለብ ስዩም

Ethio Books Delivery

ማንኛውን መጽሃፍት ይዘዙን ያለተጨማሪ ክፍያ ካሉበ እናደርስሎታለን

ለማዘዝ +251 923462526

# የመሪዎች ሴራ
# በኢትዮጵያ
## የተከዳው አማራና አዲስ አበቤ

አማራ ወደ እግዚአብሔር ጮኸ - ድምፁም እስከ አርያም ተደመጠ፤
ወያኔዎች ወደ ዲያቢሎስ ጮኹ - ድምፃቸውም እስከ ጆ ባይደን ተሰማ!




**ቀለብ ስዩም**
(የጎሊና እስረኛ)

# የመሪዎች ሴራ በኢትዮጵያ

## የተከዳው አማራ እና አዲስ አበቤ


**ቀለብ ስዩም**

የጎሊና እስረኛ



ጥቅምት 2014 ዓ.ም

መብቱ በሕግ የተጠበቀ ነው

© All Rights Reserved

ቀለብ ስዩም አበራ

የመጀመሪያ ዕትም ጥቅምት 2014 ዓ.ም

ፊደል ለቀማ፡-   ምስጋናው ጌትነት

አከፋፋይ

ዘላለም መጻሕፍት መደብር

አድራሻ፡ ፒያሳ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ጊዮርጊስ ህንፃ 1ኛ ፎቅ ዳሽን ባንክ አጠገብ

ስልክ ቁጥር፡ 0912 40 00 94/ 0912 78 45 88

# ማውጫ


መግቢያ ........................................ 15

ምዕራፍ አንድ - አይበገሬ ጀግና ህዝብ ........................................ 17

- በአማራ ላይ የሚደርሰው ጥቃት ማቆሚያው የት ነው!? ........................................ 21
- ጀኔራል አሳምነው ፅጌን ማን ገደለው? ........................................ 26
- የአማራ ሕዝብ መሪው ማነው? ........................................ 31
- አማራ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህርያቶቹ ........................................ 37
- አማራ ጠላቱ ማነው!? ........................................ 40
- የአማራ ህዝብና የወያኔ አሻጥር ........................................ 45
- "ዘላቂ ሰላም ከፈለግህ ለጦርነት ተዘጋጅ"........................................ 48
- የገባንበት ጦርነትና የተፈፀሙ ስህተቶች ........................................ 50
- ለአማራ ህዝብ ደህንነት ሲታገሉ የተገደሉ ........................................ 54
- ፋኖ አስቻለው ደሴ........................................ 61

ምዕራፍ ሁለት - የጥቁር ህዝቦች ቀን ........................................ 65

ምዕራፍ ሣስት - አዲስ አበባ እና ልዩ ጥቅም ........................................ 71

- ወያኔ—ሕወሓት በአዲስ አበባ ........................................ 78
- የምርጫው ውጤት እና የአዲስ አበባ የወደፊት ዕጣ ፋንታ........................................ 82
- የሰሜኑ ጦርነት እና አዲስ አበባ........................................ 85
- አዲስ አበቤና መፍትሄው ........................................ 88
- ባላደራውና የፊንፊኔ ሴራ ........................................ 91
- የዶ/ር አብይ የመንግስትነት አመጣጥ ሴራዎች ........................................ 93
- የጠ/ሚኒስትርነት ምርጫ ውጤት ........................................ 97

...... 102
- የኦህዴድ ልግጫ በምርጫ ...... 105
- አንብዳጁ ኢዜማ ...... 111
- የእስር ቆይታዎቼ ሰበር—ዜናዎች ...... 118
- በእስር ያሉ የጦር መኮንኖች ጥያቄ ...... 121
- ያልተለወጠው የጋዜጠኞች እስርና ሰቆቃ ...... 124
- የወንጀለኛው አንቀፅ 39 እጣ ፈንታ ...... 125
- የሻሸመኔ፣ የአጣዬ፣ የማይካድራ፣ የመተከልና የአፋር ጭፍጨፋዎች...... 130
- የትግራይጦርነት—የፖለቲካ ሽርሙጥና ውጤት ...... 133
- የሕወሓት ሰዎች በእርግጥ ሰብአዊ ፍጥረት ናቸው? ...... 149

ምዕራፍ አራት - የኢትዮጵያን ምሁራን ማን ገደላቸው? ...... 154
- ተቋማዊ ሙስና በዩኒቨርሲቲዎች ...... 160
- የሀገር አረሞች እና የፖለቲካው ባይተዋሮች ...... 164
- የኦሮሙማ አሻጥር በወለጋ ...... 173
- ሕወሃት የፈፀማቸው እልቂቶች ...... 187

ምዕራፍ አምስት - የቃሊቲ እና የቂሊንጦ ገሃነማዊ እስር ቤት እና እስረኞች...... 191
- በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ የተፈፀሙ ወንጀሎች ...... 193
- የቂሊንጦ እስር ቤት ወጎች ...... 199
- የሐሰተኛ ክስ ሰለባዋ ቀለብ ስዩም ...... 201
- የህፃናት እስር በቃሊቲ ...... 204
- የባንዳ ደባሎች ታሪክ ...... 206
- የሳማንታና የአብይ፣ የሁለት ሰዎች መግት ...... 213

ታሪካዊ ንግግሮች ...... 215

ዋቢዎች ......

# መታሰቢያነቱ፦

በሕወሓት - ኢህአዴግ እና በአርበኞች ግንቦት ሰባት ሴራ በእኔ መታሰርና በደረሰብኝ ግፍ ምክንያት ከ7 አመት በፊት ወደ ኤርትራ በርሃ ሲሄድ ተከዜ አፍነው ለሰወሩት የባለቤቴ ወንድም ለፋሲል ጌትነት ታረቀኝ እንዲሁም በሰሜኑ ሀገራችን ክፍል በተደረገው የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት ውድ ህይወታቸውን ላጡ፣ አካላቸው ለጎደለ፣ ለተፈናቀሉና ለረሃብ ለተጋለጡ ወገኖቼ ይሁንልኝ!!

# ምስጋና

በመጀመሪያ ለልዑል እግዚአብሄር እንደፈቃድህ ላኖርከኝና ከጠባቧ እስር ቤት አዩኝ አላዩኝ እያልኩ ስፅፍ አስጀምረህ ስላስጨረስከኝ ምስጋና ይግባህ።

ለውዷ እናቴ ጫቅሊት መንግስቱ ትተሽልኝ የሄድሽው ልክ የሌለው ፍቅርሽንና ጥንካሬሽን ዛሬ ላይ ከጎኔ ባትኖሪም የ መንፈስሽ ግን ለእኔ ለመንገዴ ሁሉ ብርታቴ ስለሆነኝ ውድ እናቴ ባለሽበት ሁሌም እወድሻለሁ።

ባለቤቴ በለጠ ጌትነትን ልጆቼን እናትም አባትም ሆነህ ከመንከባከብህ ባሻገር በየቀኑ ቃሊቲ እስር ቤት ተመላልሰህ የመንፈስ ጥንካሬ የሆንከኝ እንዲሁም ይህ መፅሀፍ በኮምፒተር እንዲፃፍና በመፅሃፋ ውስጥ ያሉ ታሪኮችን ለማሰባሰብ ስለረዳኸኝ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ውድ ልጆቼ ዮሐንስ በለጠ እና አቅለስያ በለጠ እናንተን ሳስብ የምገኝበት አሰቃቂ የእስር ሁኔታዬ ምንም የማይመስለኝ የእግዚአብሔር ስጦታዎቼ በየሳምንቱ እሁድ እሁድ እየመጣችሁ ንፁህ ፍቅር ስለጣችሁኝና እንድፅፍ ብርታት ስለሆናችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ።

ወንድሞቼ አቶ ባርናባስ ሽፈራውን፣ ደራሲና ጋዜጠኛ አማኑኤል አማንን፣ አቶ ለምለሙ ሰዩምን፣ አቶ ዘላለም አሳየን፣ ዶ/ር ዳንኤል ባህሩን እና ሌሎችን ለመፅሀፋን ሀሳባችሁን ስለሰጣችሁኝ ከልብ በሞቀ ምስጋና አቀርባለሁ።

እስር ቤት ሆኜ አይዞሽ እያሉ ጉልበት የሆኑኝንና መጥተው የጠየቁኝን ቤተሰቦቼን በሙሉ፣ እንዲሁም በውጭ ሀገር የምትገኙ ውድ ወንድሞቼ በሙሉ ላደረጋችሁልኝ ሁሉ በእግዚአብሔር ስም አመሰግናለሁ።

በቃሊቲ የሴቶች እስር ቤት ግቢ ውስጥ የምትገኙ ጓደኞቼ በሙሉ ለሰጣችሁኝ ልዩ ፍቅር ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። በተለይም አማረች አሸናፌ የ17 ዓመት ፍርደኛ የሆንሽው ከመጀመሪያው እስሬ የማውቅሽና ልክ እንደተንሽ እህቴ ጉርሻ ሰዩም ለኔ ዋጋ የከፈልሽ እህቴ ነሽ። በእኔ ምክንያት በካቴና እንዲሁም ለ15 ቀናት በጨለማ ቤት የታሰርሽውን መቼም አይረሳኛም። ፈጣሪዬ እንዲያሰፈታሽ ትልቅ ምኞቴ ነው።የሺመቤት ጥላሁን፣ መሰረት በድሮው እስሬ ባለውለታዬ የነበሩ ዛሬም መጥተው የጎበኙኝ ውድ እህቶቼ አመሰግናችሁዋለሁ።

ሌላው በቃሊቲ እስር ቤት ውስጥ ያላችሁ ቅኖች የፖሊስ አባላት ሁሉ ለመፅሀፋ ይረዳኝ ዘንድ መረጃ በመስጠትም ሆነ አይታችሁ እንዳላያችሁ በመሆን የበኩላችሁን የረዳችሁኝን ከልቤ አመሰግናለሁ።

# ከመጽሃፋ የውስጥ ገጾች (Highlight)

የአማራ ህዝብ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ (ብሄረሰቦች) ጋር ተዋልደና ተጋምዶ የሚኖር፣ የአማራ ህዝብ ከታላቁ የኢትዮጵያ ህዝብ (ብሄረሰቦች) ጋር ተዋልደና ተጋምዶ የሚኖር፣ በልዩነቱ የሚዋብ፣ አሣ ከውሃ ውስጥ ወጥቶ መኖር እንደማይችል ሁሉ አማራም ከኢትዮጵያዊነቱ ወጥቶ ለመኖር ይቸገራል። የአማራ ህዝብ "መነሻዬም መዳረሻዬም ኢትዮጵያ ናት" ብሎ የሚያስብ ሠፊ ህዝብ ነው። ልዩ ስጦታ፣ የማስተዳደር ችሎታም አለው፣ ጠባዬ ለስላሳ፣ ሃይማኖቱን የሚያከብር፣ እርምጃ የመውሰድ አቅም ያለው፣ የጀግንነት ባህሪይ የተላበሰ ብልጥና ተጠራጣሪ ህዝብ ነው። ሥነ-ልቦናው የዝሆንና የአንበሳን ግዙፍነት የተላበሰ ህዝብ ነው።

■■■

ጀኔራል አሳምነው ፅጌ በገራገር እይታ ሲታይ ምንም ስሜት የሌለው ይመስላል። ግን ደግሞ ልብ ብለው ሲያዩት ከሰብአዊነት አስተሳሰቡ በዘለለ እንደ ነብይ መፃኢውን ሁኔታ ከወዲሁ የመመልከት ልዩ ተሰጥኦ አለው። ለምሳሌም በአንድ ወቅት " .... የአማራ ህዝብ ከዛሬ 500 ዓመት በፊት ገጥሞት የማያውቅ ፈተና ይገጥመዋል።" ብሎ የተነበየ ጀግና ሰው ነበር። ይህ ብቻ ሳይሆን በወያኔ ስር እያለ የወያኔ አገዛዝ የማይረባ መሆኑን ቀድሞ በመረዳቱ ምክንያት አላስፈላጊውን ስርዓት ለመገርሰስ በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የከፋ እስርና ሌላም ግፍ የተቀበለ ሰው ነበር። ነገር ግን ሰፊው የአማራ ህዝብ ጀኔራል አሳምነው ፅጌን ለመረዳት የተሄደው እርቀት አነስተኛ ነበር። ከመሞቱ በፊት አይኑን ለመመልከት እድሉን ያላገኘው ሰፊው ህዝብ በተሠራው የፖለቲካ ሴራ ይህን ጀግና እንደዋዛ አጥቶታል። በተመሳሳይ መልኩ የአማራን ህዝብ መከራ በትግስት ያሻግረናል ብለን ያሰብነውን ዶ/ር አንባቸው በዚሁ ሴራ ተቀምተናል። ሌሎች ወንድሞቻችንም እንዲሁ።

■■■

ጀኔራል አሳምነው ፅጌ የአማራን ህዝብ እስራት ነበር የታሰረው። በዚህ ሁሉ እንግልት ለአማራ ህዝብ ያለው ፍቅር እንደ ሰደድ እሳት ተቀጣጠለ እንጂ አልጠፋም። ይህም ብቻ

አይደለም ውድ ሕይወቱን በአምባገነኖች ጥይት ተነጥቋል። እናም ጀኔራል አሳምነው ፅጌ ሁሌም በአማራው ህዝብ ልብ ውስጥ ይኖራል።

■■■

የአማራ ሕዝብ ደሙ፥ አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ነው። የመኖር የመጨረሻ ድንበሩ አማራነቱ ሳይሆን ኢትዮጵያዊነቱ ነው። አትንኩኝ ባይ ነው። የሌላውን መውሰድ ህሪው አይደለም። ኢትዮጵያ እጅግ ብዙ ጐርበጥባጣ መንገዶች ለዘመናት አጋጥሟት ያውቃል። እነዚህን ጐርበጥባጣ ፈተናዎችን በአባቶችና በእናቶች ጥበብና ጀግንነት እያለፈች እስከ ዛሬ ድረስ የነፃነት አርማነቷን አስከብራ የኖረች ውድ እና የተከበረች ትልቅ ሀገር ነች። እሴቷንና ባህሏን ጠብቃ መኖሯን እንኳንስ ወዳጆቿ ይቅርና ጠላቶቿ ሁሉ ያውቋታል። ኢህአዴግ ኢትዮጵያን ለ27 ዓመታት ሲገዛ በነበረበት ጊዜ እራሱ በፈጠረው የሀሰት ድርሰት፣ የሀሰት ትርክት እና መሠል አሰራሮቻቸው ውዷን ኢትዮጵያን ሲፈትኗት ኑረዋል። የተፈተነችው በባእዳን አገሮች ብቻ አይደለም፣ በራሷ ልጆች ጭምር እንጂ።

■■■

አማራ፡- የእዚህን ክፉ መንፈስ ግልፅና ስውር ጥቃት በመመከትና በመከላከል በአካልም ሆነ በአእምሮ የፈረጠመ ህዝብ እንደሆነ መመስከር ይቻላል። አማራ፥ በገነትዋ ኢትዮጵያ ልዩ ፍቅር ሁሌም የሚንበገበግ ስሜትን የታደለ፣ ውበትና እውነት ያሳደጉት፣ በሀይማኖትና በመልካም ስነ ምግባር የታነፀ፣ ፈሪሀ—እግዚአብሔር ያለው፣ በወርቃማው ህግ (Golden Rule) የሚመራ (ይህን አስተሳሰብ ላፍታታው፡ - በአንተ ላይ እንዲደረግብህ የማትፈልገውን በሌሎች አታድርግ፣ ላንተ እንዲደረግልህ የምትፈልገውንም ለሌሎች አድርግ በሚለው ንድፈ ሀሳብ የሚመራ ለማለት ፈልጌ ነው) ሌሎችን ለመጥቀም እንደ አባይ ወንዝ ርቆ የሚጓዝ፣ እንደ የሰሜን ተራሮች በታላቅ ልበ-ሙሉነት ፀንቶ የቆመ፣ የተባረከና የለመለመ ማህፀን የተቸረው፣ ጨለማን የማይወድ በጨለመበት ጊዜና ስፍራ ሁሉ የሚበራ የብርሃን ልጅ፣ የአክሱምን ሀውልቶችና የግብፅን ፒራሚዶች ያቆመ - የላሊበላንና የጎንደርን ግምብ… ያነፀ፣ እንደ ፈጣሪ አምላኩ እጅግ ታጋሽ መሀሪና ይቅር ባይ የሆነ ሕዝብ ነው።

■■■

የተከበራችሁ የእዚህ ፅሁፍ ታዳሚዎች! ገለፃዬ የአማራን ህዝብ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን ወንድሞቹ "ይበልጣል" ለማለት ፈልጌ አይደለም። በጭራሽ እንደዚያ ሊሆን አይችልም የፈለግሁት የአማራ ህዝብ ተለይቶ የሚታወቅባቸው ባህርያቶቹን ለማሳየት ነው። የኢትዮጵያን አንድነት የሚሹ ኢትዮጵያውያን ሁሉ የእዚህ የአማራ ህዝብ ታሪክ ተጋሪዎች በመሆናቸው በገለፃዬ ቅሬታ እንደማይገባቸው አምናለሁ። የኢትዮጵያን አንድነት የማይፈልጉ የጠላት ተላላኪዎችና ባንዳዎች፣ ከሀዲዎችና የእናት ጡት ነካሾች፣ የዲያቢሎስ ተሸካሚና አገልጋዮች ግን ሁሌም በውርደትና በጥፋት መንገድ የሚመላለሱ የታሪክ ተወቃሾች ናቸው።

■■■

የትናንቱ የቀዳማይ ወያኔ፣ የዛሬው ዳግማዊ ወያኔ (ሕወሓት) አላማና ፍላጎትም የራስ ሚካኤል ስሁል"ን ትንሽ የመሆን ቅዠት የተከተለ ነው ለማለት ይቻላል። ይሁን እንጂ በአማራው ህዝብ ያላሰለሰ ከፍተኛ ተጋድሎ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ሉዓላዊ የግዛት አንድነት ተከብሮ እንዲቀጥል መደረጉ የትግራዋት መሰሪዎችን በየዘመናቱ ሲያበሳጭ ኖሯል። በእዚህም ምክንያት ኢትዮጵያን ሊወር ከመጣ ጠላት ጎን በባንዳነት እየቆመ የአማራን ህዝብ ወግቷል፣ ገድሏል። የሕወሓት መሰሪዎችም የአያት ቅድመ አያቶቻቸውን ድንክዬ አስተሳሰብ ተከትለው ለአርባ አመታት ኢትዮጵያን የሑከትና የእልቂት ምድር አድርገዋታል።

■■■

በሀገር ህልውና ጉዳይ ላይ ማኩረፍና እራስን ገለልተኛ ማድረግ አይቻልም። "ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ምን አገባኝ ማለት ሲጀምር ያች ሀገር አበቃላት" ይለናል ጆን ሩስ። እናም በሀገራችን ጉዳይ ላይ ወጣቱ መርማሪ እና አስተዋይ ልብ ሊኖረው ይገባል።የቁርጥ ቀን ልጆች በመሆንም የሀገርን ችግር መቋጫ ሊዘጋጅለት ያስፈልጋል። የአርበኝነት ታሪካችንም በዚህ ትውልድ መደገም አለበት። ምክንያቱም ኢትዮጵያዊነት ማለት ሲከፋን የምንተወው ሲሞላልንም የምንቀበለው አይደለም። ኢትዮጵያ ዙሪያዋን የጨለማ አጥር ከቧታል።

■■■

የኢትዮጵያ መንግስት ግን ለህያሉ እግዚአብሔር ሙሉ በሙሉ ታዛዥና ታማኝ አልሆነም። ይህንን የምለው ያለምክንያት አይደለም። የኢትዮጵያ ጦር በሕወሓት ጦር ላይ እንዲሰለጥን ሙሉ በሙሉ በዕጁ አሳልፎ ሰጥቶት ነበር። በቅዱሳን። መፃህፍት ላይ ተፅፎ እንደሚገኘው በእግዚአብሔር ጠላቶች ላይ ዘምቶ አሰፈላጊ ርህራሔ ማሳየት ከባድ ዋጋ ያስከፍላል። ለምሳሌ የእስራኤል ንጉስ የነበረው ሳኦል የእግዚአብሔርን ጠላቶች ሙሉ በሙሉ ባለመደምሰሱና እንዳይደረግ የተከለከለውን በማድረጉ እርሱና ልጁ ዮናታን እንደዚሁም ሰራዊቱ ተደምሰሰዋል።በነብዩ ኤርሚያስም ዘመንም እንደዚሁ ተመሳሳይ ጥፋት ተፈፅሟል። እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን በእጃቸው አሳልፎ ሰጥቶ ሙሉ በሙሉ ባለመጥፋታቸው ምክንያት እስራኤላውያን በባቢሎናውያን እጅ ከፍተኛ ጥፋትና ውድመት ደርሶባቸዋል። ከጦርነቱም የተረፉትም ወደ ባቢሎን ተጉዘው ለ70 ዓመታት በባርነት እንዲማቅቁ ተደርገዋል። የነፃነትን ዋጋ የማያውቅ ህዝብ መጨረሻው እንዲህ ነው።

■■■

እኛም እንደ “ባልደራስ” አጥብቀን ከምንከራከርባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የሆነው በኦሮምኛ ትምህርት የሚሰጥባቸው ት/ቤቶች ተከፍተዋል፣ የኮንደሚኒየም ቤቶች ዕጣ ሲወጣ የኦሮሚያ ክልል ሰራተኞች ከነዋሪው ይልቅ ቅድሚያ ተሰቷቸው። የኦሮሚያ ፍርድ ቤት በአዲስ አበባ ሥራ ጀምረዋል። ኦቦ ለማ መገርሳ እንዳሉን የከተማዋን ዴሞግራፊ በመቀየር መልኩ ሰዎችን ከሌላ አካባቢዎች እያመጡ በማስፈር፣ በድርጅታዊ አሰራር በከተማዋ የኦሮምኛ ተናጋሪዎች ቁጥር እንዲጨምር ለማድረግ ተሞክሯል።

■■■

ነገር ግን ከረጅም ጊዜ ጀምሮ ከቀን ወደ ቀን እየጨመረ የመጣው የስራ አጥነት እና የኑሮ ውድነት ችግሮች ባለፈው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ጨርሰው ከቁጥጥር ውጪ እየሆኑ ነው። ስለዚህ አብዛኛው ወጣት ራሱን እና ቤተሰቡን በሕጋዊ መንገድ ማስተዳደር ሲያቅተው ወደ ሕገ-ወጥነት እና ሥርዓት አልበኝነት በፍጥነት ይገፋዋል። ይህ ደግሞ ፐለቲካዊ ውጤት ይኖረዋል ባይ ነኝ፤ “የሚበላው ያጣ ሕዝብ መሪዎቹን ይበላል” እንዲሉ ነውና። የከተማው ነዋሪ ከተሸከመው የኑሮ ውድነት ጫና ሌላ

ተጨማሪ ልዩ ጥቅም ሰበብ ከዚህ ቀደም እንዳነሳነው የከፈለው ግብር ለእርሱ አገልግሎት ሳይውል ሲቀር፣ ኮንደሚኒየም ቤቶች አይኑ እያየ ለካድሬና ከሌላ አካባቢ ለመጡ የሌላ ክልል ሰራተኞች ሲሰጡ፣ የራሱንም ስራ ተነጥቆ ከሌላ አካባቢ በመጡ ሰዎች ሲወሰድበት፣ ተወልዶ ባደገበት ከተማ ባይተዋር ሲሆን ብሶቱ እና ብስጭቱ ገንፍሎ መፈንዳቱ ሳይታለም የተፈታ እውነታ ነው። ጥያቄው "ይህ መቼ ይሆናል" የሚለው ብቻ ነው።

■■■

የኦሮሞ ወጣቶችን ብቻ ለይቶ የኢኮኖሚ ሪቮሊሽን እንዲያመጡ የሚለውን እቅድ አሁን መንግስታዊ መንበሩን ስልጣኑን ከተቆጣጠረ በኋላ በተለያየ መንገድ እየፈፀመው ይገኛል። ለምሳሌ ዶ/ር አብይ ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ከመጣ ገዜ ጀምሮ በኢትዮጵያ አረንጓዴ አሻራ በማኖር ረገድ እንደመርህ ተይዞ እየተሰራበት ይገኛል። ከልማት በፊት ክቡር የሆነውን የሰውን ልጅ ሕይወት ደህንነት መቅደም ቢኖርበትም ቅሉ በየአመቱ እጅግ ብዙ የሆኑ ችግኞችን በየቦታው ከመትከሉ ተጓዳኝ ያሉትን እውነታዎች መቃኘቱ መጥፎ አይደለም። በእርግጥም የኢትዮጵያን የአየር ንብረትም ይሁን መልከዓ-ምድሯን ለማስዋብ የተደረገው እንቅስቃሴ በመልካም ጎን የሚታይ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እነዚህ ችግኞች ከየት ነው የሚመጡ? የት ነው የሚዘጋጁት? የሚለው ጥያቄ ምላሹን አነጋጋሪ ያደርገዋል። እንደሚታወቀው እነዚህ ችግኞች መምጫቸው ኦሮሚያ ክልል መሆኑ ይታወቃል። አንድ ችግኝ በአማካይ 150-250 ብር ይሸጣል። ይህ በሚሊዮን የሚገዛ የችግኝ ብዛት በዚህ ብር ሲታሰብ፦

■■■

በአጠቃላይ ብልፅግና ፓርቲ ከካርድ አወጣጡ እስከ የምርጫ ሂደቱ እለት ይህን የጥፍነጋ አደረጃጀት ተጠቅሟል። ከዚህ ሁሉ አጠቃላይ ምስቅልቅል ሁኔታ በኋላ ምርጫውን ተውኔታዊ ይዘት በማላበስ "ኢትዮጵያ አሸነፈች" ብለው የስላቅ ብስራታቸውን አበሰሩን።

■■■

ኦሮሚያ ላይ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነጻነት እንዳይሠሩ እገታ ተደርጎባቸዋል። እናም ምርጫ ማን ከማን ጋር ተወዳድረው እንዳሸነፉ በማይታወቅበት ሁኔታ"ምርጫ" ተደርጓል። ይህ ለእኔ ህዝብን ከመናቅና ዲሞክራሲንም ከመጨፍለቅ የተለየ አይደለም።

■■■

በመሰረቱ መንግስት ለእነዚህ ሰዎች ስልጣን ቢሰጣቸው እንኳ ሹመቱ "ግንጥል ጌጥ" ከመሆን አይዘልም። በእኔ እይታና ድምዳሜ ከፋፋይ፣ ገንጣይና አስገንጣይ የሆነውን የወያኔ ህገ መንግስት ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል ፍቃደኝነቱ ከጎደለው የብልፅግናን ፓርቲ ጋር ተባብሮ ለመስራት ለመዘጋጀቱ የኢዜማን የፖለቲካ ፓርቲ ከንቱና አልባሌ ያደርገዋል ባይ ነኝ።

■■■

ባጋጣሚ እኔ ከቆምኩበት ጎን በዘመነ ወያኔ ፈላጭ ቆራጭ፣ አሳሪና ገራፊ ከነበሩት ወያኔ- ሕወሓትዎች መካከል የሰብሃት ነጋ እህት ወ/ሮ ቅዱሳን ነጋ፣ ወ/ሮ ኪሮስና ወ/ሪት ሙሉ የተባሉት ጠያቂ መጥቶላቸው ስለነበር አብረውኝ ቁመዋል። በድንገት ዞር ዞር ብለው ሲመለከቱት ጠያቂየም ግራ ተጋብቶ ምንድን ነው?" ሲል ጠየቀኝ። እኔም ያለውን ሁኔታ በዝርዝር ነገርኩትና "ወደ ወሬያችን እንመለስ" አልኩት። "ይህን ጉዳይም በደንብ ማውራት አለብን" ብሎ ተከታታይ ጥያቄዎችን አቀረበ። "አብራችሁ ነው የምትኖሩት? እንዴት ሊሆን ቻለ? ድሮ አንችን የገረፉ፣ ቶርች ያደረጉሽና ያሰቃዩ፣ ብዙ ግፍ የፈፀሙብሽ፣ በልጆችሽ፣ በባለቤትሽ ወንድምና በእናትሽ ላይ የማይረሳ ጥቁር ጠባሳ እንዲደርስ ካደረጉ ሰዎች ጋር ከአንድ ቤት አብራችሁ ታሰራችሁ?" በአንዳች ስሜት ተውጦ ለማለት የፈለገውን ሳይጨርስ ወ/ሮ ኪሪያ ኢብራሂም ተጠርታ መጣችና ተቀላቀለችን። "ማናት?" አለኝ። "አታውቃትም እንዴ? ኬሪያ ኢብራሂም የምትባለው….." ስለው በጣም ገረመው። "አይ ኢትዮጵያ ሀገራችን!" አለ።

■■■

አባይ ዘውዱ ያልተዘመረለት፣ እውነትን ብቻ የሚዘግብና የሚፅፍ ሚዛናዊ ጋዜጠኛ መሆኑን መካድ አይቻልም። በ2004 ዓ.ም በአላማ ስለተስማማን "አንድነት ለዲሞክራሲ" ከሚል ፓርቲ በአባልነት ገብተን አብረን በመታገላችንና በመቃወማችን ምክንያት፥ በቂሊንጦና ቃሊቲ እስር ቤት በእነ አንዷለም አራጌ ተሻገር በሚመሩት ብልፅግና የከፋ ምክንያት፥ በቂሊንጦና ቃሊቲ እስር ቤት በእነ አገኘሁ ተሻገር በሚመሩት ብልፅግና የከፋ እስርና እንግልት፣ ድብደባና ሌላም የከፋ ድርጊትም ተፈፅሞብናል። በታሪክ አጋጣሚ አሁንም በእስር ላይ መሆናችን እጅጉን አሳሰበኝ፣ አዘንኩም።

■■■

ጦርነቱ፥ እጅግ በጣም የከፋ ጉዳት የተፈፀመበት፣ ብዙ የሰው ልጅ ህይወት ያለፈበት፣ ብዙ የአለም አቀፍ ተራድኦ ድርጅት ሰራተኞች የሞቱበት፣ ብዙ የመከላከያ ሰራዊት አባላት በግፍ ያለቁበት፣ ብዙ አስገድዶ መድፈር የተፈፀመበትና የሌላ ሃገር ጦረኞችም የተሳተፉበት፣ እጅግ ብዙ ብዙ መውዓለ ንዋይ የፈሰሰበት፣ ብዙ የሮኬቶችና የጀት ድብደባ የተካሄደበት፣ ብዙ የወያኔ ፈላጭ ቆራጭ የነበሩ ባለስልጣናት የተገደሉበትና የታሰሩበት፣ እጅግ ብዙ ተለዋዋጭ ሁኔታዎችን ያየንበት ጦርነት ነው።

■■■

ይህ ሁሉ ሲሆን በወቅቱ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንትና የስርዓቱ አጐብዳጅ የሆነው ዶ/ር መንገሻ አድማሱ ነበር። ይህ ሰው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የጎንደር ዩኒቨርስቲ ፕሬዚዳንት፣ በኢህአፓ ጊዜ አህአፓ የነበረ በደርግም የወጣቶች ማህበር ተጠሪ የነበረ ከመጣው ጋር ሁሉ ጎንበስ ቀና የሚል ተለዋዋጭ ባህርይ ያለው ሰው ነው። በኢህአዴግ ዘመንም ለቀበሌ ምክር ቤት ሳይቀር የተወዳደረ ከመሆኑም ሌላ "የኢትዮጵያ ፕሬዚዳንት እናደርግሃለን" እያሉ የሕወሓት ባለስልጣናት ሲያታልሉትና ሙድ ሲይዙበት የነበረ ሰው ነው።

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ በሀገሪቱ የፖለቲካ ትኩሳት ዙሪያ ያጠነጥናል፡፡ ኢትዮጵያ በታሪካዊ ጠላቶችዋ አዝማችነትና በእናት ጡት ነካሽ ባንዳዎች አማካኝነት ጦርነት ተከፍቶባታል፡፡ በተለይም ጀግናውና አይበገሬው፣ እንግዳ ተቀባዩና ሩህሩሁ፣ ፍትሀዊና ሚዛን የማያጓድለው የአማራ ህዝብ የአለም አቀፉ የጥቃት ኢላማ ማዕከል ሆኖ እነሆ በመኖርና ባለመኖር አጣብቂኝ ውስጥ ገብቶ ቁምስቅሉን በማየት ላይ ይገኛል፡፡ በአራቱም ማዕዘን በህልውና ፍልሚያ ላይ ነን፡፡ ጥቃቱም መጠነ-ሰፊ ነው፡፡

በርካታ ቅን ሰዎች የጠቅላይ ሚኒስትር አብይ አህመድ መንግሥት ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ የመምራት ታሪካዊ ሀላፊነት እንደወደቀበት አድርገው ያስባሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሀገሪቱን እየገዛ ያለው ገዢ ፓርቲ (ብልጽግና) በአመለካከትም ሆነ በተግባር ከሕወሓት-ኢህአዴግ አብራክ የተገኘ መሆኑን ዘንግተውታል፡፡ በተፈጥሮ ህግ ደግሞ ከእባብ እንቁላል ርግብ አይፈለፈልም፡፡ በፖለቲካውም ቢሆን ከእዚህ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ ኢህአዴግ ሌላ ካባ (የብልጽግና ካባ) ደርቦ በመንበረ-ሥልጣኑ ዙፋን ላይ ተቀምጦ እንመለከተዋለን፡፡

የአማራ ክልሉ ገዥ (ብአዴን) ትናንት የህወሐት ተላላኪና ጥቅም አስጠባቂ ነበረ፣ ዛሬ ደግሞ "እናቴን ያገባ ሁሉም አባቴ ነው" በሚል ብሒል የኦህዴድ ተላላኪ ከመሆኑም በአሻገር ለኦህዴድ የበላይነት ተግቶ ይሰራል፡፡ ኦህዴድ በመፃኢዋ ኢትዮጵያ ውስጥ ስመ-ገናና እና ልዕለ-ሀያል ሆኖ የመቀጠል ቀቢፀ ፍላጎት አለው፡፡ ይህንን ፍላጎቱን ለማሳካትም የአማራን ህዝብ በሆነው ሁሉ ማዳከምን አይነተኛ መርህ አድርጎ ሲንቀሳቀስ እያስተዋልነው ነው፡፡ ይህ መጽሐፍ ይህን ርእሰ ጉዳይ በስፋት ይፈትሻል፡፡ በአንድ ጠጠር ሁለት ወፍ ለመግደል የሚካሄደውንም የተቀነባበረና የተጠና ፖለቲካዊ ሴራም ያጋልጣል፡፡

ዶክተር አብይ አህመድ የሚመራው የብልጽግና ካቢኔ ከወላጅ አባቱ ሕወሓት ኢህአዴግ በተማረው መሠረት የሚቃወሙትን ሁሉ እየሰበሰበ ማሰር፣ ማንገላታትና ማዋከብን ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል። እኔም የእዚሁ ጥቃት ሰለባ መሆኔም ይታወቃል።

"ዜጋ በሀገሩ ጉዳይ ላይ ምን አገባኝ ማለት ሲጀምር ያቺ አገር አበቃላት" ይለናል ጆን ሩስ። እውነት ነው፣ ባለሥልጣናት የምዕራባውያኑን ሴራ እየተቀበሉ እንደወረደ እንተግብረው ሲሉ በዝምታ ለመመልከት አንችልም።

እኔ የብልፅግናን ድብቅ ተልዕኮ ፊት ለፊት በመቃወሜ ከህፃናት ልጆቼ፣ ከምወደው ባለቤቴና ከምወዳቸው ወዳጆቼ ተለይቼ እድሜዬን በመከራና እንግልት እንዳሳልፍ መደረጌ አልጎዳኝም ለማለት አልደፍርም። ይሁን እንጂ የጠላቶቼ ዱላ የፈለገውን ያህል እስከ አጥንቶቼ ዘልቆ ቢሰማኝም፣ ነፍሴ ከሚደርስባት ስቃይ የተነሳ በውስጤ ፈስሳ ልታልቅ ብትደረስም ያመንኩበትን ከማድረግ የሚያግደኝ አንዳችም ምድራዊ ሀይል እንደሌለ እረዳለሁ። ይህ ሁሉ የበደል ናዳ የሚወርድብኝ ለሀገሬና ለህዝቤ ደህንነት በመሆኑ ይበልጥ ያጀግነኛል እንጂ ተስፋ አያስቆርጠኝም።

በአጠቃላይ ይህን መጽሀፍ ስታነቡ በእዚህች ታሪካዊና እድሜ-ጠገብ ሀገር ውስጥ እነማን ምን እያደረጉ እንዳሉ ትረዳላችሁ ብዬ አስባለሁ። ውድ ወገኖቼ! በማንኛውም ጊዜም ሆነ ስፍራ ለክፉዎችና መሠሪዎች አታጎብድዱ፣ ክፉውን ተቃወሙ፣ ለድምፅ አልባዎች ድምፅ ሁኑ፣ በፍቅር ተመላለሱ፣ በእውነትና በፍትሀዊነት ኑሩ፣ እናንተ በፈጣሪ አምላክ ጥላ ስር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ናችሁ፣ ምንም በእናንተ ላይ እንዲሰለጥን ራሳችሁን የሌላው ባርያ ለማድረግ አትፍቀዱ።

የዚህ መጽሐፍ አላማም ሆነ ተልዕኮ ይኸው ነው። መልካም ንባብ!!

ቀለብ ስዩም አበራ


ቃሊቲ የህሊና እስረኛ/ አዲስ አበባ

ጥቅምት/2014 ዓ/ም

# ምዕራፍ 1

# አይበገሬ ጀግና ህዝብ

## የደራሲዋ ቀደምት ሥራ






በነገራችን ላይ በጀኔራል አሳምነው ፅጌ የሰለጠነው የአማራ ልዩ ኀይልና ሚሊሻ የአማራና የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅነቱን እንሆ በተግባር በማሳየት ላይ ይገኛል፡፡ ከነዚህ አጠቃላይ ሁኔታ ተነስቼ ጀኔራል አሳምነው ፅጌን ደግሜ ደጋግሜ ባወድሰውና ባጀግነው ያንስበታል እንጂ አይበዛበትም፡፡ ደከመኝ፣ ሰለቸኝ የማይል የማይዝል ሃይል ነው፡፡

■ ■ ■

የብአዴን አመራሮች ወያኔን ለማስደሰት ሲሉ በአማራው ህዝብ ደም እጃቸውን ታጥበዋል፡፡ በአንፃራዊነት ሲታይ የኦህዴድ አመራሮች ከብአዴን እጅግ በተሻለ መልኩ ለህዝባቸው ተቆርቋሪዎች ነበሩ ለማለት ይቻላል፡፡

■ ■ ■

ኦሮሚያ ላይ ተፎካካሪ ፓርቲዎች በነጻነት እንዳይሠሩ እገታ ተደርጎባቸዋል፡፡ እናም ምርጫ ማን ከማን ጋር ተወዳድረው እንዳሸነፉ በማይታወቅበት ሁኔታ "ምርጫ" ተደርጓል፡፡ ይህ ለእኔ ህዝብን ከመናቅና ዲሞክራሲንም ከመጨፍለቅ የተለየ አይደለም፡፡

■ ■ ■

በአጠቃላይ ይህን መጽሀፍ ስታነቡ በእዚህች ታሪካዊና እድሜ-ጠገብ ሀገር ውስጥ እነማን ምን እያደረጉ እንዳሉ ትረዳላችሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ ውድ ወገኖቼ! በማንኛውም ጊዜም ሆነ ስፍራ ለክፋዎችና መሠሪዎች አታጎብድዱ፣ ክፋውን ተቃወሙ፣ ለድምፅ አልባዎች ድምፅ ሁኑ፣ በፍቅር ተመላለሱ፣ በእውነትና በፍትሀዊነት ኑሩ፣ እናንተ በፈጣሪ አምላክ ጥላ ስር የምትኖሩ ኢትዮጵያውያን ናችሁ፣ ማንም በእናንተ ላይ እንዲሰለጥን ራሳችሁን የሌላው ባርያ ለማድረግ አትፍቀዱ፡፡


Printing by Gola Publishing Service
+251 911 65 86 31



ዘላለም መጻሕፍት መደብር
0912400094


ዋጋ ሁለት መቶ ሃያ ብር ብቻ
ዋጋ 220.00 ብር ብቻ



Ethio Books Delivery

# Ethio Books Delivery

## WORLD WIDE DELIVERY

online order books and take delivery